# ለትራንዚተሮች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈተና ተሰጠ

በአስቴር ልሳኑ

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና በንግዱ ማህብረሰብ መካከል ድልድይ ሆነው ለሚያገለግሉ ትራንዚተሮች/አስተላላፊዎች ባለፈው ግንቦት 10/2002 ዓ.ም. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈተና ተሰጠ፡፡

ለትራንዚተሮቹ ከፈተናው በፊት ለሁለት ሳምንታት በተለያዩ ጉምሩክ ነክ ጉዳዮች ላይ ባለስልጣኑ ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ የጉምሩክና የታክስ ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር በሁለት ዙር ስልጠና ሰጥቷቸዋል፡፡

የፈተናው አላማ የትራንዚተሮችን ሙያዊ ብቃት በማሳደግ ወደ ህጋዊ መስመር ለማስገባት እንደሆነ በባለስልጣኑ የደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወ/ሮ ሰናይት ስዩም ጠቁመዋል፡፡ በቀጣይም ስልጠናው ለሌሎች ትራንዚተሮች እንደሚሰጥ አስታውቀዋል፡፡

አንዳንድ ትራንዚተሮች ስልጠናውም ሆነ ፈተናው ለስራቸው አስፈላጊ ሆኖ እንዳገኙትና ወደፊትም ማንኛውም ስልጠና ቢዘጋጅላቸው የመሰልጠን ፍላጎት እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡